ግንቦት 20 ቀን 2020 ሁን

ውድ ወላጅ(ጆች) እና/ወይም ሞግዚት(ቶች)፣

የ Columbia (ኮሎምቢያ) ግዛት (ግዛቱ) ነጻ እና ዋጋቸው ቅናሽ የሆኑ ምግቦችን የሚያገኙ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ትምህርት ቤት ዝግ ሆኖ በሚቆይበት ጊዜ ጤናማ ምግቦችን ማግኘት መቀጠላቸውን ለማረጋገጥ ይተጋል። ይህ ደብዳቤ የተጻፈው የ US የእርሻ ዲፓርትመንት (US Department of Agriculture, USDA) የቤተሰቦች የመጀመሪያ የኮሮናቫይረስ ምላሽ ህግ ላይ ያለውን የወረርሽኝ ጊዜ የኤሌክትሮኒክ የጥቅማጥቅም ማስተላለፊያን (Pandemic Electronic Benefit Transfer, P-EBT) እንዲተገብር ፍቃድ ማግኘቱትን ለመግለጽ ነው። P-EBT በአገር አቀፍ የትምህርት ቤት የምሳ ፕሮግራም (National School Lunch Program, NSLP) መሰረት ነጻ ወይም ዋጋቸው ቅናሽ የሆኑ ምግቦች የሚያገኙ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ይሰጣል። እነዚህ ቤተሰቦች ትምህርት ቤት እያሉ በመደበኛነት ያገኙ የነበረውን የምግብ ዋጋዎች ለመደጎም፣ ለህዝብ ጤና አደጋ ምላሽ የመስጠት አካል የሆነውን፣ የምግብ ጥቅማጥቅሞች ያገኛሉ። የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ቁርስ እና ምሳን ለመሸፈን የታቀዱ እና በሳምንት ለአንድ ልጅ $28.50 ዋጋ ያላቸው ናቸው። P-EBT በግዛቱ ላሉ ከ68,000 በላይ ላሉ ልጆች $26 ሚሊዮን ግምት ያለው የፌደራል የምግብ እርዳታ ይሰጣል።

ነጻ ወይም ዋጋቸው ቅናሽ የሆነ የትምህርት ቤት ምግብ ለማግኘት ብቁ የሆነ ማንኛውም የግዛቱ ልጅ የ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን ያገኛል። ይህ ለሁሉም ተማሪዎች ነጻ ምግብ በሚያቀርብ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ልጆችን ያካትታል። **በተጨማሪ የገቢ ለውጥ ያጋጠማቸው ቤተሰቦች ያሏቸው ልጆች፣ አስቀድሞ ነጻ ወይም ዋጋቸው ቅናሽ የሆኑ ምግቦችን አግኝተው የማያውቁ ቢሆንም ለ P-EBT ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።** እነዚህ ቤተሰቦች ለ FARM ብቁ ከሆኑ P-EBT ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የነጻ እና ዋጋቸው ቅናሽ የሆነ የምግብ ማመልከቻ (Free and Reduced-price Meal, FARM) ለመሙላት ትምህርት ቤታቸውን በተቻለ ፍጥነት ማግኘት አለባቸው። ለ FARM ብቁ የሆኑ አዲስ ቤተሰቦች ማረጋገጫ ከተሰጣቸው ወር ጀምሮ እስከ ጁን 19 P-EBT ያገኛሉ። ከጁን 19 በኋላ የተረጋገጡ የFARM ማመልከቻዎች ለP-EBT ብቁ አይሆኑም።

የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ሜይ ላይ መሰጠት ይጀምራሉ። የተጨማሪ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (Supplemental Nutrition Assistance Program, SNAP) ወይም የችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (Temporary Assistance for Needy Families, TANF) ጥቅማጥሞች የሚያገኙ ቤተሰቦች ያሏቸው የግዛቱ ልጆች፣ ከመደበኛ ወርሃዊ ጥቅማጥቅሞች በተጨማሪ፣ በቤተሰቡ የኤሌክትሮኒክ የጥቅማጥቅሞች ማስተላለፊያ (Electronic Benefits Transfer, EBT) ካርድ ላይ ተጨማሪ ክፍያ ይሞላላቸዋል። SNAP ወይም TANF የማያገኙ፣ ወይም የሚሰራ የ EBT ካርድ የሌላቸው ቤተሰብ ያሏቸው የግዛቱ ልጆች፣ የ P-EBT ጥቅማጥቅሞች የተሞላለት የ EBT ካርድ በፖስታ ይላክላቸዋል። ገንዘቡን ለማግኘት ይህ አዲስ የ EBT ካርድ እንዲሰራ መደረግ ይኖርበታል። እነዚህ ቤተሰቦች P-EBT መጠቀም ካልፈለጉ፣ በፖስታ የደረሳቸውን አዲስ የ EBT ካርድ ማስወገድ አለባቸው።

እንደ SNAP ጥቅማጥቅሞች፣ የ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን ለ SNAP ፍቃድ ያላቸው የችርቻሮ ነጋዴዎች ጋር ምግብ ለመግዛት ወይም ከአማዞን ኦንላይን ለማዛዝ amazon.com/snap-ebt መጠቀም ይቻላል። የ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን የሚያገኙ ኗሪዎች በአቅራቢያቸው ያሉ ለ SNAP ፍቃድ ያላቸውን የችርቻሮ ነጋዴዎችን fns.usda.gov/snap/retailer-locator በመጎብኘት ሊያገኙ ይችላሉ።

እባክዎ በዚህ እሽግ ውስጥ ስለ P-EBT አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና መልስ እና የመረጃ በራሪ ጽሁፍ ያግኙ። በተጨማሪ፣ ስለ ግዛቱ የ P-EBT ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ኦንላይን በ dhs.dc.gov/p-ebt ወይም የ P-EBT የጥሪ ማእከል ጋር በ (202) 868-6663 ከ 7:30 ጥዋት -4:45 ከሰዓት፣ ከሰኞ – ዓርብ በመደወል ማግኘት ይችላሉ።

P.O. Box 91920, 64 New York Avenue, NE • Washington DC 20002
P 202.671.4200 F 202.671.4326 • DHS.DC.GOV

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR